# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY
PUBLIC SCHOOLS

ተያያዥ ግብአቶች: JEA-RB
ሃላፊነት ያለበት ቢሮ: Deputy Superintendent of Schools
ተያያዥ ምንጮች: የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ §10.06.04.03፣ የሚያስፈልጉ ክትባቶች

## በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተላላፊ በሽታ ቁጥጥር

I. ዓላማ

በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ለመርዳት።

II. ትርጉም

A. ደም እና የሰውነት ፈሳሾች ለተላላፊ በሽታዎች አስተላላፊ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ የሰውነት ክፍሎች ናቸው። የደም እና የሰውነት ፈሳሾች የአሞኒቲክ ፈሳሾች ፣ሰገራ ፣ደም ፣የደም ውጤቶች ፣የጡት ወተት ፣ ሴሬብሮስፒናል ፈሳሽ ፣ የወር አበባ ደም ፣ የአፍንጫ ፈሳሾች ፣ የፔሪቶናል ፈሳሽ ፣ ፔዩራል ፈሳሽ ፣የፍሳሽ ማስወገጃ ፣ምራቅ ፣የዘር ፈሳሽ ፣ሲኖቪያል ፈሳሽ ፣እንባ ፣ሽንት ፣የሴት ብልት ፈሳሽ ፣ትውከት, እና የቁስል ፍሳሽ ናቸው።

B. ደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን በሰው ደም ውስጥ ወይም በሰውነት ፈሳሾች ውስጥ የሚገኙ እና በሰዎች ላይ በሽታ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጥቃቅን ህዋሳት ናቸው።

C. የሚያጋልጠው በሽታን ሊያስተላለፍ ከሚችል አስተላላፊ ሰው፣ አካባቢ ወይም የተበከለ ነገር ወይም አካባቢ ጋር መገናኘት ነው።

D. በሽታ መከላከል አንድ ሰው በተፈጥሮ የሰውነት መከላከያዎች ወይም በክትባት ምክንያት ተላላፊ በሽታን የመቋቋም ሁኔታ/አቅም ነው።

E. መደበኛ ጥንቃቄዎች በደም ወለድ እና በሌሎች በሽታ አምጪ ተህዋሲያን የመተላለፍ አደጋን ለመቀነስ በበሽታ ቁጥጥር እና መከላከያ ማእከል (ሲዲሲ) የሚመከሩ መመሪያዎች ናቸው። ለደም፣ ለሁሉም የሰውነት ፈሳሾች፣ ሚስጥራቶች፣ ልቀቶች (ደም ቢይዙም)፣ ያልተነካ ቆዳ እና የ mucous membranes/ንፍጥ አመንጭዎች ላይ ይተገበራሉ። የጥንቃቄ እርምጃዎች ከታወቁት እና ከማይታወቁ የኢንፌክሽን ምንጮች የሚመጡ ረቂቅ ተሕዋስያን ስርጭትን ለመቀነስ የተነደፉ ናቸው።

F. ተላላፊ በሽታ በአንድ የተወሰነ ተላላፊ ወኪሉ ወይም በመርዛማ ምርቶቹ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። ወኪሉ ወይም ምርቶቹ በበሽታው ከተያዘ ሰው፣ እንስሳ ወይም ግዑዝ ማጠራቀሚያ ወደ ተጋላጭ አስተናጋጅ/ተቀባይ በማስተላለፍ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመካከለኛው ተክል ወይም የእንስሳት አስተናጋጅ፣ ቬክተር ወይም ግዑዝ አካባቢ ይከሰታል።

III. መነሻ-ዳራ

A. በትምህርት ቤት አካባቢ የተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት ለመቆጣጠር የሚረዱ ዘዴዎች ውስንነቶች/ገደቦች አሏቸው። ብዙ በሽታዎች ከመከሰታቸው በፊት ተለይተው የሚታወቁ ምልክቶች ወይም በጠቅላላው መተላለፊያ ጊዜ ውስጥ ምንም ምልክት ሳይታይባቸው የሚተላለፉባቸው/የሚስፋፉባቸው ጊዜያት አሏቸው። በመሆኑም ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ወይም ለመቆጣጠር የሚደረገው ጥረት ቀጣይነት ባለው መልኩ መቀጠል ይኖርበታል።

B. ከሁሉም ግለሰቦች ለደም እና ለሰውነት ፈሳሾች መጋለጥ ለደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን እንደ ተላላፊነት ሊቆጠር ይገባል። መደበኛ ጥንቃቄዎች ከደም እና ከሰውነት ፈሳሾች የሚመጡ ኢንፌክሽኖችን የመተላለፍ እድልን ለመቀነስ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው (የMontgomery County Public Schools [MCPS] የደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋስያን ተጋላጭነት መቆጣጠሪያ ዕቅድን ይመልከቱ)። እነዚህ ጥንቃቄዎች ትክክለኛ የእጅ መታጠብ እና እንደ ጓንት፣ ጭንብል፣ የአይን መከላከያ፣ የፊት መከላከያ፣ የላብራቶሪ ኮት ወይም ጋውን እና/ወይም ከአፍ ወደ አፍ መተላለፍ/መሂድን ለመቆጣጠር የመከላከያ መንገዶችን ከደም ወለድ በሽታ አምጪ ንጥረ ነገሮችን ጨምሮ ተገቢውን ማስወገድ የመሰሰሉ የግል መከላከያ መሳሪያዎችን መጠቀምን ያካትታሉ። የMCPS የደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋስያን ተጋላጭነት መቆጣጠሪያ እቅድ በስራ ደህንነት እና ጤና አስተዳደር/በሜሪላንድ የስራ ደህንነት እና ጤና (OSHA/MOSH) ደንብ 29CFR 1910.1030 መሰረት በደም ለሚይዙ ወይም የሰውነት ፈሳሾች ተጋላጭነትን ለመቀነስ እና/ወይም ለማስወገድ ሂደቶችን ይዘረዝራል። እነዚህ ሂደቶች ህጉን ለማክበር መተግበር አለባቸው።

C. የሜሪላንድ ግዛት ተማሪዎች በተወሰኑ ተላላፊ በሽታዎች ላይበተማሪዎቹ ዕድሜ እና ደረጃ ላይ በመመስረት የክትባት ማረጋገጫ እንዲያሳዩ ይፈለጋል።ለአንዳንድ በሽታዎች የመከላከል አቅምን ለመጠበቅ በሃኪም እንደሚታዘዘው በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ቡስተር/ተጨማሪ የክትባት መጠን አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የትምህርት እና የጤና አገልግሎት ሰራተኞች ተማሪዎችን፣ ወላጆችን እና ማህበረሰቡን እንደዚህ አይነት ክትባቶች የበሽታ መከላከል እና ደህንነት አስፈላጊ አካል መሆናቸውን በንቃት እና በቀጣይነት ማስተማር አለባቸው።

IV. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል በጣም አስፈላጊው ዘዴ እጅ መታጠብ ነው። ተማሪዎች እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች ሳሙና እና ውሃ በመጠቀም ትክክለኛውን እጅ መታጠብ እንዲለማመዱ ይበረታታሉ። ሳሙና እና ውሃ ከሌለ አልኮልን መሰረት ያደረጉ የእጅ ማጽጃዎችን መጠቀም ይቻላል።

B. አመታዊ የደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን ስልጠና በትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች በ OSHA/MOSH ደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን መመሪያዎች መሰረት ይካሄዳል። ይህ አመታዊ የደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋስያን ስልጠና የሚካሄደው ሰራተኞቹ እራሳቸውን ከበሽታ ሊያስከትሉ ከሚችሉ ጥቃቅን ተህዋሲያን ለመከላከል እርምጃዎችን እንዲተገብሩ፣ ሁለንተናዊ ጥንቃቄዎችን እንዲያደርጉ እና የደም መፍሰስን በአግባቡ ለማጽዳት እንዲችሉ ነው። የMCPS የደም ወለድ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን ፕሮግራምን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት የደህንነት ተቆጣጣሪ፣ የፋሲሊቲዎች አስተዳደር መምሪያ ነው።

C. የት/ቤቱ ማህበረሰብ ጤና ነርስ (SCHN) የቁጥጥር እርምጃዎችን እንዲጀምር/እንዲዘጋጅበት እና እንደአስፈላጊነቱ ሪፖርቶችን ለማቅረብ እንዲመች በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ ስለሚገኙ ተላላፊ በሽታ

ጉዳዮች ሁሉ ማወቅ ይገባል።

D. አንድ ተማሪ ተላላፊ በሽታ እንዳለበት ሲጠረጠር በተላላፊ በሽታዎች ማጠቃለያ፡ መሰረት እርምጃዎች ይወሰዳሉ። የትምህርት ቤት እና የህጻናት እንክብካቤ መመሪያ፣ በጤና እና የአእምሮ ጢና መምሪያ (DHMH) ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል www.edcp.org/html/cd_guide.html። DHMH የእውነታ መረጃዎችwww.edcp.org/html/cdindex.htmከወላጆች እና ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር ሊጋራ ይችላል።

E. SCHN እንደ አስፈላጊነቱ የበሽታ መቆጣጠሪያ፣ የተላላፊ በሽታ እና ኤፒዲሚዮሎጂ (ሲዲ እና ኢ)፣ የህዝብ ጤና አገልግሎት፣ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ሰራተኞችን ያማክራል። እሷ/እሱ ርእሰመምህሩን/ሯን ስለ አስፈላጊ ክትትል፣ ለምሳሌ ከትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ከወላጅ ማህበረሰብ እና/ወይም ከተማሪዎች ጋር የጽሁፍ ግንኙነት በመሳሰሉ ጉዳዮች ምክር ይሰጣል/ትሰጣለች፣ እና ስለተወሰኑ የቁጥጥር እርምጃዎች ለMCPS ሰራተኞች የጤና ትምህርት እና ምክር ትሰጣለች።

F. በሲዲ እና ኢ ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ምንጩን፣ ሌሎች እውቂያዎችን እና የኢንፌክሽን ስርጭትን ሁኔታ ለማወቅ እና በቂ የጤና ጥንቃቄዎች መኖራናቸውን ለማረጋገጥ ጠቃሚ በሽታዎችን ይመረምራል። ተጨማሪ ስርጭትን ለመከላከል ይረዳል።

G. ሁለቱም ትምህርት ቤት፣ የትምህርት እና የጤና ሰራተኞች የክትባት አስፈላጊነትን እንደ የበሽታ መከላከል እና ደህንነት አስፈላጊ አካል ተማሪዎችን፣ ወላጆችን እና ማህበረሰቡን በንቃት እና በቀጣይነት ያስተምራሉ። ሁሉም ተማሪዎች በሜሪላንድ ግዛት ክትባት በትምህርት ቤቶች እና በቅድመ ትምህርት ፕሮግራሞች ለተመዘገቡ ህፃናት መስፈርቶች ክትባት መከተባቸውን ለማረጋገጥ በትብብር ይሰራሉ።

የደንብ ታሪክ፡ የቀድሞ ደንብ ቁጥር 5256፣ ጥቅምት የተሻሻለ 1982 ዓ.ም. መጋቢት 18 ቀን 2008 ዓ.ም የተሻሻለ።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ጁን 2022